287

የሰ/መ/ቁ. 27161

ኅዳር 12 ቀን 2000

ዳኞች፡- መንበረፀሐይ ታደሰ

ፍስሐ ወርቅነህ

መስፍን እቁበዮናስ

ተሻገር ገ/ሥላሴ

አብዱራሂም አህመድ

አመልካች፡- አቶ ኤልያስ ከፈለ - አልቀረበም፡፡

ተጠሪ፡- እነ አቶ ከድር አህመድ /4 ሰዎች/ ቀረቡ፡፡

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

ይህ የሰበር አቤቱታ የቀረበው አመልካች ጥቅምት 3 ቀን 1999 ዓ.ም. ጽፎ ባቀረበው ማመልከቻ መነሻነት ነው፡፡

የጉዳዩን የሥር አመጣጥ የአሁን ተጠሪዎች በፌዴራሉ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በአመልካች ላይ ያቀረቡት ክስ በቂርቆስ ክ/ከተማ የሚገኘውን የንግድ ቤት ለኑሮአቸው መቋቋሚያ ተፈቅዶላቸው መንቀሳቀሻ ገንዘብ በማጣት ላሁኑ አመልካች ቦታውን ለ4 ዓመት ማከራየታቸውን፣ ውሉ ከተደረገ በኋላ ቦታው የተሰጣቸው ለዘለቄታው ሣይሆን ለ3 ዓመት ብቻ መሆኑን መገንዘባቸውንና በቦታው ላይ ከብረታ ብረት ወርክሾፕ በስተቀር ሌላ ሥራ መሥራት እንደማይችሉ፣ ከዚህ ውጭ ሠርተው ከተገኙ የሊዝ ውሉ የሚሠረዝ መሆኑ በአስተዳደር አካል የተነገራቸው መሆኑን፣ አመልካች ግን ከሊዝ ውሉ ውጭ እየሠሩ ስለሚገኙ በውሉ ለመቀጠል አስቸጋሪ ሁኔታ ከመፈጠሩም በላይ ከክ/ከተማው ጋር ባረደረጉትም ውል ለሌላ ሶስተኛ ወገን ቦታውን አሣልፎ መስጠት የተከለከለ በመሆኑ ባጠቃላይ ውሉ የተሣሣተ ውል ነው ተብሎ እንዲሠረዝ የሚል ነው፡፡ አመልካችም መልስ እንዲሰጡ በተታዘዙበት እለት ባለመቅረባቸው በጽሁፍ መልስ የመስጠት መብታቸው ታልፏል፡፡ ከዚህ በኋላ ግራ ቀኙ የቃል ክርክር እንዲያቀርቡ ተደርጎ ፍርድ ቤቱ አመልካችና ተጠሪዎች ያደረጉት ውል ከሊዝ ውሉ ጋር የማይጣጣም ነው በማለት ውሉን ሠርዞ ግራ ቀኙ ወደየነበሩበት እንዲመለሱ ሲወስን የከፍተኛው ፍርድ ቤትም በይግባኝ ውሣኔውን አጽንቷል፡፡ አመልካች ይህን የሰበር አቤቱታ ያቀረቡት በዚህ መነሻነት ሲሆን ፍ/ቤቱም አቤቱታውን መርምሮ መልስ ሰጪን በማስቀረብ ግራ ቀኙን አከራክሯል፡፡ ክርክራቸውንም ከሕጉ ጋር በማገናዘብ መርምሯል፡፡

በዚህም መሠረት ግራ ቀኙ ያደረጉት ውል ከሕዳር 6 ቀን 1996 ዓ.ም. ጀምሮ ለአራት ዓመት ማለትም እስከ ኀዳር 6 ወይም 7 ቀን 2000 ዓ.ም. ድረስ የሚዘልቅ መሆኑን ፍርድ ቤቱ ተረድቷል፡፡

በሌላም በኩል ተጠሪዎች ከቂርቆስ ክ/ከተማ ጋር ያደረጉት የሊዝ ውል ለሶስት ዓመታት የሚዘልቅ መሆኑን ተጠሪዎች በክሣቸው ላይ ገልፀዋል ተጠሪዎች ካቀረቡት ክስ በመነሣት ፍርድ ቤቱ ለመገንዘብ የቻለው ጉዳይ በክርክር ሒደት ላይ እያለ የሊዝ ውሉ የጊዜ ገደብ ያበቃ መሆኑን ነው፡፡ የሊዙ የጊዜ ገደብ ካለቀ ደግሞ ተጠሪዎች የነበራቸውን የክስ መሠረት ያጡ ስለሆኑ አጠያያቂነት የለውም በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 280 ላይ እንደተመለከተው ክሱ በማንኛውም ደረጃ ባለ ጊዜ የክሱ መሠረት ማክተሙን ፍርድ ቤቱ ከተረዳ ክሱን እንደሚሠርዝ በግልጽ ተደንግጓል፡፡ በተያዘውም ጉዳይ ተጠሪዎች ለሶስት

ዓመት ከክፍለ ከተማው ጋር ያደረጉት ውል ማብቃቱ የተረጋገጠ ስለሆነና በዚህም ሣቢያ በቦታው ላይ ምንም አይነት መብት ስለሌላቸው፣ በሌላም በኩል አመልካችም በውሉ ከተመለከተው የአራት ዓመት ጊዜ በላይ በቦታው የተጠቀመ ስለሆነ ግራ ቀኙን መብት በሌላቸው ጉዳይ እየተከራከሩ መሆኑን ፍርድ ቤቱ በመገንዘቡ የሥር ፍርድ ቤቶች የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት መሆን አለመሆኑን ማየት ሣያስፈልግ የሰበር አቤቱታውን ሠርዘናል በተመሣሣይ ሁኔታም ተጠሪዎችን ተጠቃሚ ያደረገው የሥር ፍርድ ቤቶች ውሣኔም ከላይ በተመለከተው ምክንያት ከእንግዲህ ተፈፃሚ ሊሆን አይችልም ብለናል፡፡



**ኔ**

- የሰበር አቤቱታው ተሰርዟል፣ የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤትና በዚህ ጉዳይ የተጀመረው የአፈፃፀም መዝገብ እንዲዘጋ ታዟል፡፡
- ግራ ቀኙ ወጪያቸውን ይቻሉ፡፡
- መዝገቡ ተዘግቷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ነ/ዓ



/መ/ቁጥር 28923

ግንቦት 7 ቀን 2000 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** ዓብዱልቃድር መሐመድ

ተገኔ ጌታነህ

መድሕን ኪሮስ

ዓሊ መሐመድ

ሱልጣን አባተማም

**አመልካች፡-** የባህር ዳር ጨርቃጨርቅ አክስዮን ማሕበር አልቀረቡም

**ተጠሪዎች፡-** 1ኛ/ የባህር ዳር ልዩ ዞን አስተዳደር አልቀረቡም

2ኛ/ የመንግሥት የልማት ድርጅቶች ባለአደራ ቦርድ ነገረፈጅ

አቶ አዳነ መጋቡ ቀረቡ፡፡

መዝገቡ የተቀጠረው ለምርመራ ነበር፡፡ መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

**ፍ ር ድ**

መዝገቡ የቀረበው አመልካች የአማራ ብሔራዊ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ጥር 4 ቀን 1999 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ በማለት የካቲት 5 ቀን 1999 ዓ.ም